የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

<u>የካቲት 28 ቀን 2010 ዓም</u>

# ጀግና ጥቃትን ከመቀበል መስዋዕትን የመረጡ!!

*ለውድ ኢትዮጵያውያን!!*

*በትላንትናው ዕለት የመቶ አለቃ ደርቤ የአጋዚን ጀሌ ሰራዊት ረፍርፈው ለኢትዮጵያ ሀገራቸውና ለኢትዮጵያዊው ወገናቸው መተኪያ የሌላት ሕይወታቸውን አሳልፈው መስጠታቸውን መግለጻችን ይታወሳል፤ በአባቶቻችን አባባል ጀግና ጀግንነቱ የሚገለጸው ለዓላማው ሲሰዋ ብቻ ነው፤እንዳሉት ሁሉ መኮንኑ የተጣለባቸውን አደራ ሙሉ ለሙሉ ተወጠዋል፤ ጀግናው የመቶ አለቃ ደርቤ በደርግ አስተዳደር ጊዜ በውትድርና አገራቸውን ሲያገለግሉ የነበሩ ሲሆን ሰራዊቱ ሲፈርስ ውስጥ ውስጡን ፀረ ወያኔ ትግል ሲያደራጁ ቆይተዋል፥ ሁኔታውን የተጠርጠረ ወያኔ ትጥቃቸውን ሊያስፈታቸው ወደ መኖሪያ ቤታቸው ዘለቀ፣ መኮንኑ ከወያኔ ተላላኪዎች ጋር ከአምስት ሰዓት በላይ ቤታቸውን ከብቦ ሲታኮስ ከነበረ ወያኔ ትላንት እንደገለጽነው ወያኔ ስምንት ጀሌዎቹን ሲያጣ ሠላሳ አምስት ከፉኛ ቆስለውበት ነበር፣ ከቆሰሉትም መካከል እስከ ዛሬ ቀትር ድረስ አምስት ሲሞቱ በአጠቃላይ የሚቆች ቁጥር እስከአሁን አስራ ሦስት መድረሱን ከአከርባቢው ቃል አቀባያችን የተረጋገጠ መረጃ ደርሶናል፣ እንዲሁም የጀግናው የመቶ አለቃ ደርቤ ባለበት በትኩሱ መካከል ቆስለው ከሆስፒታል እንደሚገኙ ከአከባቢው መረጃ አረጋግጦልናል፣ የጀግናው የመቶ አለቃ ደርቤ የቀብር ሥነሥር አት ወዳጅ ዘመድ እንዲሁም የትግል አጋሮቻቸው በተገኙበት በታላቅ ክብር ተፈጽሚል፤*

*በዛሬው ዕለት ጀግናው ሕዝባችን የመቶ አለቃ ደርቤን አርማ በማንሳት በጸረ ወያኔ ትግሉ እንደሚቀጥል ኢሕብፓ እና ኦሕን ኢአ ወገናዊ ጥሪያቸውን ያቀርባሉ!!*

*የ ኢትዮጵያ አንድነት በልጆቿ ደን ለዘላዓለም ተከብሮ ይኖራል!!*

*ኢትዮጵያዊ ሁሉ በያሉበት የመቶ አለቃ ደርቤን ፈለግ ይከተል ዘንድ ጥሪያችን እናቀርባለን!!*

## *ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!*

| | |
|---|---|
| ኢሕብፓ<br>EPNP<br>የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ<br>ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY | ኦሕንኢአ<br>OPMEU |

EPNP.INFO

ኢሕብፓ
EPNP
የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY



EPNP

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY